የዩኤስ አሜሪካ የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስቴር
አለም አቀፍ የሠራተኛ ጉዳይ ቢሮ
ህጻናት የጉልበት ሠራተኞች፡ የግዳጅ ስራ፡ እና የሰዎች ሕገወጥ ዝውውር ቢሮ

አስፈጻሚ ትዕዛዝ 13126
በተገደዱ ወይም በውል በተገደቡ ህጻናት የጉልበት ሠራተኞች የሚመረቱ ምርቶች ዝርዝር

# ኢትዮጵያ

## ጨርቃ ጨርቅ

ኢትዮጵያ ውስጥ በጨርቅ ሽመና ምርት ላይ ተገደው የሚሠሩ ሕጻናት በአብዛኛው እድሚያቸው እስከ ሰባት አመት የሚደርሱ ወንዶች ልጆች እንዳሉ ዘገባዎች ያሳያሉ። እነዚህ ሕጻናት ብዙውን ጊዜ የሚሰሩት አዲስ አበባ ውስጥ ሲሆን አብዛኛዎቹ የሚመጡት የጎምንፋን እና የወላይታን ዞኖች ጨምሮ ከደቡብ ነው። አንዳንዶቹ በሕገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ሰለባነት ነው። በሕገወጥ የሚዘዋወሩ ሕጻናት አብዛኛውን ጊዜ ለመልማዮች የሚሸጡ ሲሆን ወላጆቻቸው እና ሕጻናቱ ለሚሰሩበት የሚገባቸውን ክፍያ እና የመማር እድል እንደሚሰጥ የሃሰት ቃል እየተገባላቸው ይጭበረባራሉ። አንዳንዶቹ ሕጻናት ሥራ ቦታ ይተኛሉ። እንዲሁም ተለይተው እና በግድ ተይዘው በቂ ምግብ ሳያገኙ ይቆያሉ። እነሱም የአካል ጉዳት እየደረሰባቸው ይቀጣሉ ። አንዳንድ ሕጻናት ረጅም ሰዓታት እና ትርፍ ጊዜ እንዲሰሩ እየተገደዱ የሚከፈላቸውም ከሆነ በጣም አነስተኛ ክፍያ ይሰጣቸዋል።

የቤተሰባችሁን ብድር መክፈል አለባችሁ እየተባሉ ሕጻናቱ ክፍያ የሚሰጣቸው እንኳዋን ቢሆን በጣም አነስተኛ ክፍያ ነው የሚያገኙት። በተጨማሪ ብዙዎቹ የተቀበሩ ፈንጂዎች በሚታወቁ የጦር መኮንኖች እና በታጠቁ ቡድኖች ቁጥጥር ስር ሲሆኑ ሕጻናትን ጨምሮ መንደሮችን እየከበቡ መሳሪያ በመደቀን፤ በዛቻ እና በማስፈራራት አስገድደው ያሠሩቸዋል። እነዚህ ተገደው የሚመለመሉ ሕጻናት የመንቀሳቀስ ነፃነት የሌላቸው ሲሆን ለሥራቸውም ክፍያ አያገኙም።